DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

# የቤት አልባዎች የትምህርት መርሐግብር፦
## የቤት አልባነት ችግር ላጋጠማቸው ወላጆች እና ተማሪዎች የትምህርት የመማር መብት

ልጅዎ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት እንዳለው ያውቃሉ? የቤት አልባነት ያጋጠማቸው ቤተሰቦች McKinney-Vento Homeless Assistance Act በሚባለው የፌደራል ሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ልጅዎ የትምህርት ዕድል ለማግኘት ያለውን መብት ማወቅ አስፈላጊ ነው።

የቤት-አልባ ልጆችና ወጣቶች ምን ዓይነት መብት አላቸው?




ቤት-አልባነት የገጠማቸዉ ተማሪዎች ይህ መብት አላቸው፡

- ምንም እንኳን የትምህርት ቤት መዝገቦች፣ የሕክምና መዛግብት፣ ወይም ትምህርት ቤቶች በምዝገባው ወቅት የሚጠይቋቸዉ ሌሎች ሰነዶች ባይኖራቸዉም; የመመዝገብ፣ ትምህርት የመከታተል፣ እና በሁሉም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ።
- በትምህርት ቤት ዉስጥ ስኬታማ ለመሆን ለእነሱ የሚጠቅማቸዉ ከሆነ በመጡበት ትምህርት ቤት ወይም ቤት-አልባ ከመሆናቸዉ በፊት በመጨረሻ በነበሩበት ትምህርት ቤት የመቆየት።
- ለልጅ ወይም ለወጣት የተሻለ ጥቅም ካለዉ; ቤተሰቡ በአሁኑ ሰዕት ከሚኖርበት ቦታ ቅርብ ከሆነው ትምህርት ቤት መማር።
- አስፈላጊ ከሆነ፣ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ እና ለመመለስ የመጓጓዣ እርዳታ የማግኘት::
- ዩኒፎርም መልበስ የትምህርት ቤቱ ግዴታ ከሆነ የዩኒፎርም እርዳታ የማግኘት።.
- የትምህርት ቤቱን የቤት-አልባ ረዳት ተጠሪዎችን የሕክምና፣ የጥርስ፣ የአእምሮ እና ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን የመጠየቅ።

ለቤት-አልባ ልጆችና ወጣቶች ምን ዓይነት ድጋፍ እና እርዳታዎች ይሰጣሉ?

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ ቤት-አልባ የሆኑ ተማሪዎችን በምዝገባ፣ ትምህርታዊ ዉሳኔዎችን በማድረግ ቤተሰቦች ለመርዳት እና ቤት-አልባነትን የገጠማቸዉን ቤተሰቦች ለመደገፍ ሀላፊነት ያለበት ረዳት ተጠሪ አለ። አንዳንዶቹም ድጋፎች ለትምህርት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን፣ የህክምና፣ የጥርስ እና ሌሎች አገልግሎቶች እርዳታ፤ እና የነጻ የትምህርት ቤት ምግብ ያካትታሉ። እንዲሁም ቤት-አልባ ለሆኑ ተማሪዎችን የረዳት ተጠሪው ወደ ትምህርት ቤት ደርሶ መልስ መጓጓዣን ሊያዘጋጅ ይችላል። ቤት-አልባ ለሆኑ ተማሪዎች የረዳት ተጠሪዎች ስም ዝርዝር በ ኦኤስኤስኢ (OSSE) ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል https://osse.dc.gov/service/homeless-education-program-district-columbia-homeless-liaisons-contact-list.

የወላጅ ሃላፊነት ምንድን ነው?

ከ 5-7 እድሜ ያሉ ልጆችዎ በትምህርት ቤት መመዝገባቸዉንና መከታተላቸዉን ማረጋገጥ ሀላፊነትዎ ነዉ እንዲሁም የአካባቢ ሕግ ያስገድዶታል። በልጅዎ ት/ቤት ውስጥ በአካባቢው የቤት-አልባ ግንኙነት ሀላፊ ለማወቅ ካስቸገረዎ ወይም ልጅዎን ሊያስመዘገቡት ከፈለጉ ኦኤስኤስኢ (OSSE) HEP.OSSE@dc.gov ወይም (202) 654-6123 አሁኑኑ ያግኙ።.

## በትምህርት ቤት ምርጫ ወይም ምደባ ላይ አለመግባባት ቢነሳስ?

በትምህርት ቤት ምርጫ ወይም ምደባ ላይ አለመግባባት ከተፈጠረ፣ ትምህርት ቤቱ

- አለመግባባቱ እስከሚፈታ ድረስ በወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ብቻዉን በሆነ ወጣት መግባት በሚፈለግበት ትምህርት ቤት ልጆቹን ወይም ወጣቱን ማስገባት አለበት።.
- ለወላጁ፣ አሳዳጊዉ ወይም ብቻዉን ለሆነዉ ወጣት የትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔን እና የይግባኝ መብቶችን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። የጽሑፍ ማስታወቂያዉም የትምህርት ቤቱን ውሳኔ ምክንያቶችን ይዘረዝራል።
- ብቻዉን የሆነውን ወጣት፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የአለመግባባቱን መፍታት ሂደት በጊዜዉ መወጣት ወዳለበት ወደ ቤት-አልባ ለሆኑ ተማሪዎችን የረዳት ተጠሪ መምራት።
- በአከባቢያው ደረጃ ሊፈቱ ያልቻሉትን አለመግባባቶችን ወደ ኦኤስኤስኢ (OSSE) በኢ-ሜይል Transitory.Services@dc.gov ወይም ፋክስ ወደ (202) 299-2136 ወዲያዉኑ መተላለፋን ያረጋግጡ። ለተጨማሪ እርዳታ፣ (202) 654-6123 ይደዉሉ።

ስለ መከኒ-ቨንቶ **McKinney-Vento Homeless Assistance Act** ተጨማሪ መረጃ**:** የመከኒ-ቨንቶ (McKinney-Vento) ኤምኬቪ (MKV) የቤት-አልባ የእርዳታ አዋጅ የቤት-አልባ ለሆኑ ተማሪዎች የትምህርት መብታቸውን የሚጠብቅ የፌደራል ህግ ነዉ። በቅርቡ፣ ኤምኬቪ (MKV) በ እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል አዋጅ (Every Student Succeed Act of 2015 (ESSA)) ዳግም የተፈቀደለት የእያንዳንዱን የቤት-አልባ ህጻን መሰናክሎችን ለማስወገድ እና የትምህርት ፍላጎታቸውን ለማሟላት የድጋፍ አገልገሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ነው።.

የቤት-አልባነት ማለት**:**

ኤምኬቪ (MKV) የቤት-አልባ ልጆችን “ቋሚ፣ የዘወትር እና በቂ (ተቀባይነት ያለው) የማምሻና የማደርያ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች” ብሎ ይገልጸዋል። አዋጁ በዚህ ትርጉም ስር የሚጠቃለሉትን በምሳሌነት ከዚህ በታች ይዘረዝራል፡

- በመኖሪያ ቤት ማጣት፣ በኢኮኖሚያዊ (በገንዘብ) ችግር ወይም በተመሳሳይ ምክንያት የሌሎች ሰዎች ቤትን የሚያጋሩ፤ በአሁኑ ሰዐት ሌላ ምርጫ ስለሌላቸዉ በአልቤርጎ፣ ሆቴሎች፣ መኪናዎች፣ በመናፈሻ ቦታዎች ውስጥ የሚያድሩ፤ በአስቸኳይ ሁኔታ ወይም በጊዜያዊ መጠለያ (የዲሲ የሽግግር መኖሪያን ጨምሮ) የሚኖሩ ወይም በሆስፒታሎች ዉስጥ የተተዉ ህጻናትና ወጣቶች፤
- በመኪናዎች፣ መናፈሻዎች፣ የሰው መኖርያ ያልሆኑ የግል ወይም ህዝባዊ ቦታዎች፣ በባዶ ሕንፃዎች፣ የአውቶብስ ወይም የባቡር ጣቢያዎች፣ ወይም ጥሩ ባልሆኑ ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩ ሕጻናት እና ወጣቶች፤
- ከላይ በተገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ ስለሚኖሩ ቤት-አልባ ለመባል ብቁ የሆኑ መንገደኛ ልጆች፤ እና
- ብቸኛ፣ በወላጅ ወይም አሳዳጊ አካላዊ ጥበቃ ሥር ያልሆኑ ወጣቶችን፣ እና ከዚህ በላይ በተገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ በሙሉ ቤት አልባ ለመባል ብቁ ናቸው::

የ ኦኤስኤስኢ**(OSSE)** የቤት-አልባ የትምህርት ፕሮግራም ኤችኢፒ **(HEP)** ተልዕኮ**:** የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት ኦኤስኤስኢ(OSSE) የቤት-አልባ የትምህርት ፕሮግራም ኤችኢፒ(HEP) ተልዕኮ እያንዳንዱን የቤት-አልባ ህጻን እና ወጣት ነጻ፣ ተገቢ፣ የሕዝብ ትምህርት እድሎችን እንደሚያገኝ ማረጋገጥ፤ ለትምህርት ቤቶች፣ ለመጠለያዎች እና ለማህበረሰቡ ስልጠናና ድጋፍ መስጠት፤ እና የቤት-አልባ ለሆኑ ቤተሰቦች ስለሚገጥሟቸዉ ችግሮች ለሕብረተሰቡ ማሳወቅ ነው። የቤት-አልባ ለሆኑ ቤተሰቦች በጥሩ ሁኔታ መደገፋቸዉንና ተማሪዎችን ለመደገፍ ተገቢ ገንዘብ መሰጠቱን ያረጋግጣል፡ ኦኤስኤስኢ (OSSE) የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት አዋጅ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) መሰረት ስለተማሪው ሁኔታ ከትምህርት ቤቶች ጋር በመደበኛነት መረጃን ያካፍላል።

መኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) የፌደራል መመሪያዎች እና ፖሊሲዎች ላይ መመሪያ ለማግኘት፣ እባክዎ በዚህ ያግኙን፡-
ወይዘሪት ኒኮል ሊ-ሙዋንዳ፣ ሆምለስ ኢዱኬሽን ስቴት ኮርድኔተር
Nicole.Lee-Mwandha@dc.gov ወይም (202) 654-6123

ምዝገባ፣ ትራንስፖርት፣ ስልጠና እና የማህበረሰብ ተደራሽነት ላይ ድጋፍ ለማግኘት፣ እባክዎን በዚህ ያግኙን፦
አቶ ታሺን ስታሊንግስ፣ ሆምለስ ኢዱኬሽን ፕሮግራም አናሊስት
Tasheen.Stallings@dc.gov or (202) 478-5927

ከመኪኒ-ቬንቶ የእርዳት ፈንዶች እና ደንብ ማስከበሮች ላይ እገዛ የሚሹ ከሆነ፣ እባክዎ በዚህ ያግኙን፦
ወይዘሪት ዳኔሊ ሮሊንስ፣ ሆምለስ ኢዱኬሽን ፕሮግራም አናሊስት
Danielle.Rollins@dc.gov or (202) 741-0255